# በፌዴራል አስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 ላይ የተዘጋጀ ሥልጠና

ሰለሞን ጌታቸው

# አዋጅ ቁጥር 1/1987 ሕገ-መንግስታዊ

**አንቀጽ - 9 የሕገ መንግስት የበላይነት**

ማንኛውም ሕግ፣ ልማዳዊ አሠራር፣ እንዲሁም የመንግሥት አካል ወይም ባለሥልጣን ውሳኔ ከዚህ ሕገ መንግስት ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

ማንኛውም ዜጋ፣ የሕገ መንግሥት አካላት፣ የፖለቲካ ድርጅት፣ ሌሎች ማኅበራት እንዲሁም ባለሥልጣኖቻቸው፣ ሕገ መንግሥቱን የማስከበርና ለሕገ መንግሥቱ ተገዥ የመሆን ኃላፊነት አለባቸው።

ኅዳር 29 ቀን 1987

- **አንቀጽ - 12 - የመንግስት አሠራርና ተጠያቂነት**
  - የመንግስት አሠራር ለሕዝብ ግልጽ በሆነ መንገድ መከናወን አለበት፡፡
  - ማንኛውም ኃላፊ የሕዝብ ተመራጭ ኃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂ ይሆናል፡፡
- **አንቀጽ - 37 ፍትሕ የማግኘት መብት**
  - ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው፡፡
- **አንቀጽ - 50 ስለ ሥልጣን አካላት አወቃቀር**
  - የፌዴራል መንግስት የሕግ አውጪነት የሕግ አስፈፃሚነትና የዳኝነት ሥልጣን አላቸው

- **አንቀጽ - 72 ስለአስፈጻሚነት ሥልጣን**
  - **የኢትዮጵያ ፌዴራል መንግስት ከፍተኛ የአስፈጻሚነት ሥልጣን የተሰጠው ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ነው።**
- **አንቀጽ - 77 የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር**
  - **የሚኒስቴሮችንና በቀጥታ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ተጠሪ የሆኑ ሌሎች የመንግስት አካላትን አደረጃጀት ይወስናል ሥራቸውን ያስተባብራል ይመራል**
- **የፌዴራል አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 1263/2014**

- ተቋማት ሲደራጁ የተሰጣቸውን ተግባርና ሀላፊነት ለመወጣት በሚያስችል መልኩ ...
- ... ኃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል የአስፈፃሚ አካላት አደረጃጀት መፍጠር አሰፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤
- ሚኒስቴር፣ ኮሚሽን፣ ባለስልጣን፣ አስተዳደር ወይም ልማት፣ አገልግሎት፣ ጽሕፈት ቤት እና ኢንስቲትዩት
- 22 ሚኒስቴር መ/ቤት
- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላት እንደገና ለማደራጀት የወጣው አዲስ አዋጅ 24 የሚሆኑ ተቋማትን በካቢኔ ደረጃ

❖ በመመሪያ አወጣጥ ሂደት የነበሩና ያሉ ችግሮች፤

- ...መመሪያው ሲዘጋጅ አሳታፊ አለመሆን፤ ሚስጥራዊነት፤ ቢሮ ዘግቶ በባለሙያ ብቻ ማርቀቅ፤
- ...የሚወጣው መመሪያ በአስተዳደር መስሪያ ቤቱ ሥልጣን ክልል ስር ስለመሆኑ ማረጋገጫ አለመኖር፤
- ...መመሪያዎች በቅርጽና በይዘት ወጥነት የሌላቸው መሆን (መመሪያ፤ ማንዋል፤ ሠርኩላር፤ ጋይድላይን ወዘተ..)
- ...መመሪያው ከጸደቀ በኋላ ለተገልጋይ ተደራሽ አለመሆን (ቆልፎ ማስቀመጥ)
- ...ከአስተዳደር መስሪያ ቤቱ የሥልጣን ክልል ውጪ መመሪያ ወጥቶ ቢገኝ ማን፤ ምን ማድረግ እንዳለበት፣ አለመታወቅ፤
- ---መመሪያው ውድቅ ከተደረገ ውጤቱ ምን እንደሆነ አለመታወቅ፤ ውድቅነቱ ለተያዘው ጉዳይ ብቻ ወይስ

- የአስተዳደር ህግ፡- ስልጣን እና ተግባር የሚደነግጉ ሕጎች
  - የመንግስትና የዜጎችን ግንኙነት የሚገዙ ሕጎች
  - ተጠያቂነትን የሚደነግጉ
- የአስተዳደር ስ/ሕግ፡- የአስተዳደር አካላት የአስተዳደር ተግባራት አሰጣጥ ስርዓተን ይደነግጋል
- የአስተዳደር ተቐማት፡- ሕግ የማውጣት
  - የማስፈፀም
  - የመተረጎም ስልጣን አላቸው

-የስልጣን ክፍፍል መርህን ይጥሳል;

# የአስተዳደር መመሪያ

- የፌዴራል አስተዳደር ሥነ ሥርዓት ሕግ ለፌዴራል አስተዳደር ተቋማት የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነትን እንዴትና መቼ እንደሚያከናውኗቸው የሚደነግግ ሕግ ነው ማለት ነው፡፡
- መመሪያ ማለት ሕግ አውጪው አካል በሚሰጠው የውክልና ስልጣን መሰረት በአስተዳደር ተቋም የሚወጣና በሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ ውጤት የሚያስከትል የሕግ ሰነድ ሲሆን በስራ ላይ ያለ መመሪያን የሚያሻሽል ወይም የሚሽር የሕግ ሰነድንም ይጨምራል፡፡

- አስተዳደር ተቋም፡-

  አስፈጻሚ አካል ሆኖ በሕግ የተደራጀ የመንግሥት መሥሪያ ቤት እና ለፌደራል መንግሥት ተጠሪ የሆነ የከተማ አስተዳደር

- የተፈፃሚነት ወሰን

-በዐቃቤ ሕግ

-ፖሊስ

-መከላከያ

-ደህንነት

➢ አገልግሎት መስጠትና ቁጥጥር ሲያረጉ

# መመሪያ ስለማውጣት

- ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም መመሪያ ማውጣት ይችላል
- ማንኛውም ሰዉ መብቱን ወይም ጥቅሙን ማግኘት አለበት
- ማንኛዉም የአስተዳደር ተቋም የሚገባዉን አገልግሎት ወይም አስተዳደራዊ ዉሳኔ ላለመስጠት መመሪያ አልወጣም ምክንያት ሊሆን አይችልም፡፡

# መመሪያ ስለሚወጣበት ጊዜ

- በእናት ህገ አስገዳጅ ሲሆን - በሦስት ወራት
- አስገዳጅ ባልሆነ ሁኔታ - በተገቢው ጊዜ ውስጥ
- መመሪያ እንዲወጣ በጽሁፍ ጥያቄ ማቅረብ
- በሠለሳ የሥራ ቀናት ውስጥ መመሪያውን የማውጣት ሂደት መጀመር ወይም ምክንያቱን በመግለጽ ጥያቄውን ውድቅ ማድረግ አለበት፡፡

# የቅድመ መመሪያ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት

- መዝገብ ማደራጀት

  ሀ) በተቋሙ በመታየት ላይ ያለ ረቂቅ መመሪያ ርዕሰ ጉዳይ እና የመመሪያውን አወጣጥ መርሃ ግብር፤

  ለ) የረቂቅ መመሪያው ዝግጅት በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ የሚያመለክት መረጃ፤

  ሐ) ረቂቅ መመሪያውን በተመለከተ የታተሙ ማስታወቂያዎች፤

  መ) በረቂቅ መመሪያው ላይ አስተያየት ስለሚቀርብበት ጊዜ፤

  ሠ) ረቂቅ መመሪያውን በተመለከተ የተሰበሰቡ አስተያየቶችንና በአስተዳደር ተቋሙ በአስተያየቶቹ ላይ የተወሰዱ አቋሞችን፡፡

- ማንኛውም ሰው የሚደራጀውን መዝገብ መመልከት ወይም አስፈላጊውን ወጪ ሸፍኖ ቅጂውን መውሰድ ይችላል፡፡

# ማስታወቂያ ስለማዉጣት

- ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ እና የተቋሙን ድረ ገጽ ጨምሮ በሌሎች የመገናኛ ብዙሃን ማስታወቂያ ማውጣት አለበት

  ፩/ የመመሪያውን ረቂቅ ለማዘጋጀት መሰረት የሆነውን ሕጋዊ ሥልጣን እና በመመሪያው ስለሚካተቱት ርዕሰ ጉዳዮች፤

  ፪/ የረቂቅ መመሪያውን ቅጂ ማግኘት የሚቻል ስለመሆኑና የሚገኝበትን ሁኔታ

  ፫/ በረቂቅ መመሪያው ላይ ሰዎች አስተያየታቸውን መቼ እና እንዴት ሊያቀርቡ እንደሚችሉ፤

  ፬/ መዝገብ ላይ የሰፈሩ መረጃዎችን የትና መቼ ማግኘት እንደሚቻል የሚገልፅ መረጃ፡፡

02/19/2026 02:24 PM

# ረቂቅ መመሪያን ለአስተያየት ስለመላክ

- የአስተዳደር ተቋም ለሕዝብ ያሳወቀውን ረቂቅ መመሪያ ለሚመለከታቸው የአስተዳደር ተቋማትና ለሌሎች ባለድርሻ አካላት ለአስተያየት መላክ አለበት
- የሚመለከታቸው የአስተዳደር ተቋማትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በረቂቅ መመሪያው ላይ አስተያየት ካላቸው አስተያየታቸውን ተቋሙ በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ በጽሁፍ መላክ አለባቸው፡፡
- ተቋሙ የሚወስነው የጊዜ ገደብ በማናቸውም ሁኔታ ከ፲፭ የሥራ ቀናት ማነስ የለበትም።

# የውይይት መድረክ ስለማዘጋጀት

- የአስተዳደር ተቋሙ በመመሪያው ረቂቅ ላይ የጽሑፍ አስተያየት መቀበያ ጊዜ ካበቃ በኋላ መመሪያው ከመፅደቁ በፊት ማንኛውም ሰው የሚሳተፍበት የውይይት መድረክ ማዘጋጀትና ግብዓት መሰብሰብ አለበት፡፡
- በግብዓት ማሰባሰብያ መድረክ ያልተሳተፈ ማንኛውም ሰው አስተያየቱን በጽሑፍ ጭምር ሊያቀርብ ይችላል፡፡
- የአስተዳደር ተቋሙ በሚያዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ አስተያየቶችን ማስተናገድ የሚያስችል በቂ ጊዜ መመደብ አለበት፡፡

# ከሥነ-ሥርዓት ነጻ ስለመሆን

- ሥነ-ሥርዓት ነጻ ሊሆን ይችላል፦

  ሀ) የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ በመኖሩ በግዴታዎቹ ሥርዓት ውስጥ ለማለፍ ጊዜ የማይፈቅድ ሲሆን፤

  ለ) ቅድመ ማስታወቂያ ማውጣቱ የሕዝብን ጥቅም የሚጎዳ ሆኖ ሲገኝ፤ ወይም

  ሐ) ቅድመ ማስታወቂያ ማውጣቱ የመመሪያውን ተፈጻሚነት ፋይዳ ቢስ የሚያደርግ ሲሆን።

- የአስተዳደር ተቋም መመሪያ ሲያወጣ ከግዴታ ነጻ እንዲሆን ያደረገውን ምክንያት የያዘ ዝርዝር መግለጫ ማዘጋጀት አለበት።

# መመሪያ ስለማጽደቅና ስለተፈፃሚነቱ

- **መመሪያ ስለሚጸድቅበት ጊዜና ሁኔታ**
- የአስተዳደር ተቋሙ በተዘጋጀው መመሪያ ረቂቅ ላይ የተወሰነው የጽሑፍ አስተያየት ማቅረቢያና የውይይት መድረክ ማካሄጃ ጊዜ እስኪያልፍ ድረስ መመሪያውን ማጽደቅ አይችልም፡፡
- የአስተዳደር ተቋሙ መመሪያውን ከማጽደቁ በፊት በረቂቁ ላይ የቀረበ አስተያየት ከግምት ወስጥ ማስገባት አለበት።
- የአስተዳደር ተቋሙ በአስተያየቱ መሠረት ማስተካከያ ማድረግ አለበት ወይም አስተያየቱን የማይቀበል ከሆነ፣ የማይቀበልበትን ምክንያት የሚያብራራ ጽሑፍ ማዘጋጀት አለበት፡፡

- የአስተዳደር ተቋሙ ረቂቅ መመሪያውን ከማጽደቁ በፊት ለአስተያየት ለፍትህ ሚኒስቴር መላክ አለበት፡፡
- ፍትህ ሚኒስቴር በረቂቅ መመሪያው ላይ ያለውን አስተያየት በ፲፭ የሥራ ቀናት ውስጥ ለአስተዳደር ተቋሙ መላክ አለበት፡፡
- ፍትህ ሚኒስቴር በዚህ የጊዜ ገደብ ውስጥ አስተያየቱን ካልላከ አስተያየት እንደሌለው ተቆጥሮ መመሪያውን የማጽደቁ ሂደት ይቀጥላል፡፡

# በመመሪያው ረቂቅና በሚወጣው መመሪያ መካከል ልዩነት ስለመኖር

- የአስተዳደር ተቋሙ በማስታወቂያ ከተመለከተው ረቂቅ መመሪያ ጋር መሠረታዊ ልዩነት ያለው መመሪያ ማዉጣት አይችልም፤
- በመጨረሻ መልክ የተዘጋጀ መመሪያ በማስታወቂያ ከተመለከተው የመመሪያው ረቂቅ መሠረታዊ ልዩነት አለው ሊባል የሚችለው፦

  ሀ) የረቂቅ መመሪያው የተፈጻሚነት ወሰን በጉልህ የተለወጠ ከሆነ፤ ወይም

  ለ) ረቂቅ መመሪያው አዳዲስ ግዴታዎችን አካትቶ የተገኘ ከሆነ።

# የማብራሪያ ጽሑፍ

- ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም መመሪያ በሚያወጣበት ጊዜ የሚከተሉትን መረጃዎች የያዘ የመመሪያው ማብራሪያ ማዘጋጀት አለበት፦
  - ፩/ መመሪያው የወጣበት የሕግ መሠረትና ዓላማ፤
  - ፪/ በማስታወቂያው የተሰራጨው ረቂቅና የመጨረሻ ሆኖ በወጣው መመሪያ መካከል የይዘት ልዩነት ካለ የተደረጉትን ለውጦች ከነምክንያቶቹ የሚገልጽ ማስታወሻ
  - ፫/ በረቂቅ መመሪያው ላይ የቀረቡ አስተያየቶችና የተወሰዱ እርምጃዎች ማጠቃለያ።

02/19/2026 02:24 PM

# የመመሪያ ይዘትና ቅርፅ

- በአስተዳደር ተቋም የሚወጣ ማንኛዉም መመሪያ የሚዘጋጀው በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ ሲሆን ከመመሪያው ዋና ይዘት በተጨማሪ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፦

1. የመመሪያው ተራ ቁጥር፤
2. መመሪያው እንዲወጣ የሥልጣን ምንጭ የሆነውን ሕግ፤
3. የመመሪያውን አጭር ርእስ፤
4. ትርጓሜ፣ የተፈፃሚነት ወሰን፣ ዋና ዋና ድንጋጌዎች፤
5. የማሻሻያ ፣ መሻሪያ፣ መሸጋገሪያ፣ ማቆያ ድንጋጌ ካለ ይህንኑ የሚመለከት ድንጋጌ፤
6. መመሪያው የወጣበትንና ተፈጻሚ የሚሆንበትን ቀን።።

02/19/2026 02:24 PM

- ማንኛውም መመሪያ በአጭርና በግልጽ ቋንቋ መጻፍ አለበት፡፡
- የአስተዳደር ተቋም ሌላ አካል ያወጣቸውን በሥልጣኑ ክልል የሚወድቁ መመሪያዎች ወይም የሥነ-ምግባር ደንቦች በሙሉ ወይም በከፊል በማጣቀስ የራሱ መመሪያ አካል ማድረግ ይችላል፡፡
- የመመሪያው አካል ያደረጋቸውን ሰነዶች ለሕዝብ ተደራሽ ማድረግና እንዲመዘገብ ለፍትህ ሚኒስቴር መላክ አለበት፡፡



# የመመሪያ ምዝገባ

- ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም መመሪያ እንዳወጣ ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት መመሪያውን ከነማብራሪያው ለፍትህ ሚኒስቴር በመላክ እንዲመዘገብ ማድረግ አለበት፡፡
- ፍትህ ሚኒስቴር የተላከለትን መመሪያ ቁጥር ሰጥቶ ይመዘግባል።
- መመሪያው ስለመመዝገቡም ለአስተዳደር ተቋሙ ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

- የፍትህ ሚኒስቴር የመዘገበውን መመሪያ ከነማብራሪያው መዝግቦ ለአስተዳደር ተቋሙ ካሳወቀበት እለት ጀምሮ ለሕዝብ ክፍት ማድረግ አለበት።

- ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በሥራ ላይ የነበረ መመሪያን ይህ አዋጅ በወጣ ከ፺ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለፍትህ ሚኒስቴር በመላክ እንዲመዘገብ ማድረግ አለበት።

02/19/2026 02:24 PM



# የመመሪያ ተደራሽነት

- የፍትህ ሚኒስቴር በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፰ መሠረት የመዘገበውን መመሪያ በድህረ ገጹ ላይ መጫን አለበት፡፡
- ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም ያወጣውን መመሪያ፦
  - ሀ) አሰትሞ ለሚመለከታቸው መንግስታዊና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ማሰራጨት፤ እና
  - ለ) በተቋሙ ድህረ ገጽ ላይ መጫን፤ አለበት፡፡
- ማንኛውም የመመሪያውን ቅጂ ማግኘት የሚፈልግ ሰው መመሪያውን ባለበት ሁኔታ የመመልከት ወይም ወጪውን ሸፍኖ ከአስተዳደር ተቋሙ የማግኘት መብት

# የመመሪያ ተፈጻሚነት

- ያልተመዘገበ እና በአስተዳደር ተቋሙ ድህረ ገጽ ላይ ያልተጫነ መመሪያ ተፈጻሚነት አይኖረውም።
- ተፈጻሚነቱን ያጣ መመሪያ ተፈፃሚነት እንዲኖረው የቅድመ መመሪያ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት ተከትሎ እንደ አዲስ እንዲወጣ ሊደረግ ይችላል።

# ስለመመሪያ ተፈጻሚነት ግምገማ

- ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም ያወጣውን መመሪያ አፈጻጸም በተመለከተ በየጊዜው እየገመገመ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡

------------------//////-------------------

# አስተዳደራዊ ውሳኔ

- የአስተዳደር ውሳኔ መስጠት እና መፈፀም የአስተዳደር ተቋሞች ከተፈጥሮ ባህሪያቸው የሚመነጭ የዕለት ተዕለት ዋነኛ ተግባር ነዉ፡፡
- የአስተዳደር ውሳኔ ማለት የአስተዳደር ተቋም በዕለት ተዕለት ተግባሩ በሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ የሚሰጠዉ ዉሳኔ ነዉ፡፡
- መብት ወይም ጥቅም የተባለዉ በሕግ የታወቀ ሆኖ ገንዘብ ነክ ወይም ገንዘብ ነክ ያልሆነ ሊሆን ይችላል፡፡

# የአስተዳደር ዉሳኔ አሰጣጥ መርሆዎች

- **በሕግ የተሰጠ ሥልጣን ወሰንን አለማለፍ** - የተቋሙ የሥልጣን እና የተግባር
- **የግል እና የሕዝብ ጥቅምን ማመዛዘን** - ሁለቱ ጥቅሞች እንዲጣጣሙ
- **አግባብነት በሌለዉ ጉዳይ ወይም ፍላጎት አለመመራት** - ለተቋሙ ባቀረበዉ የዉሳኔ ይሰጥልኝ ጥያቄ እና በአስተዳደር ተቋሙ ዓላማ
- **ሙያዊ ውሳኔ መስጠት** - እውቀት፤ ክህሎት እና ሥነ-ምግባር
- **ማዳመጥ/መስማት** - ፍሬ ነገር፤ የህግ መሠረት እና ማስረጃ በሚገባ ማዳመጥ እና መመርመር

02/19/2026 02:24 PM

- **በቅን ልቦና መወሰን** - የባለጉዳዩን መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት እያሰቡ አለመወሰን
- **በቂ ምክንያት መስጠት** - መፍቀድም ሆነ መከልከል በበቂ ምክንያታዊ ትንታኔ የተደገፈ መሆን ይገባዋል።
- **የጥቅም ግጭትን ማስቀረት** - የጉዳዩን ፍሬ ነገር፤ የህግ መሠረት እና ማስረጃ ገለልተኛ ሆኖ መመርመር እና መወሰን
- **የተገልጋዮችን እኩልነት ማክበር** - ከማንኛውም መድሎአዊ አሰራር የመጠበቅ
- **በተገቢዉ ጊዜ መወሰን** - የተንዛዛ አሠራር እንዳይኖር ማድረግ
- **ተገማች መሆን** - በፍሬ ነገር፤ በህግ መሠረት እና በማስረጃ ተመሳሳይ የሆኑ ጉዳዮችን በተመሳሳይ መወሰን

# የአስተዳደር ዉሳኔ አፈፃፀም

- የአስተዳደር ዉሳኔዉን ለተገልጋዩ መስጠት
- የአስተዳደር ዉሳኔዉ የተገልጋዩን መብት ወይም ጥቅም ሥራ ላይ የሚያዉል፤ የሚያሻሽል ወይም የሚከለክል ሊሆን ይችላል፡፡

- **በአስተዳደር ዉሳኔ ላይ የሚቀርብ ቅሬታ**

- ዉሳኔ ለሰጠዉ ተቋም ቅሬታ የማቅረብ መብት

# የቅሬታ ማስተናገጃ አካል ማቋቋም

- የተቋሙ ቋሚ አካል ሆኖ የሚቋቋም ነዉ፡፡
- ለተገልጋዮች ይፋ ማድረግ አለበት፡፡

## ➢የአስተዳደር ዉሳኔዉ አፈፃፀም መታገድ

- ቅሬታዉን መመርመርና መወሰን
- በቅሬታዉ ላይ የተሰጠዉን ዉሳኔ ለተገልጋዩ መስጠት

-------------------//////-----------------

# የፍርድ ቤት ክለሳ ሥነ-ሥርዓት

- የመጨረሻ በሆነ የአስተዳደር ውሳኔ
- አስተዳደራዊ መፍትሄዎች አሟጦ መጨረስ

➢ የክለሳ አቤቱታን ለማየት ሥልጣን የተሰጠው ፍርድ ቤት

- ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት
  - የአስተዳደር ውሳኔ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ነው፡፡
  - የአስተዳደር መመሪያ ላይ ይግባኝ ሊቀርብበት ይችላል፡፡

# የክለሳ ምክንያቶችና መርሆዎች

- በአዋጁ ክፍል ሁለት እና ሦሥት የተመለከቱትን የሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎች ሳይከተል የወጣ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

- የአስተዳደር መመሪያ በተጨማሪ፡-
- ከአስተዳደር ተቋሙ የሥልጣን ገደብ ውጪ የወጣ ሲሆን፣ ወይም
- በእርከን ከመመሪያ በላይ ከሆኑ ሌሎች ሕጎች የሚቃረን ሲሆን ነው፡፡

# በአስተዳደር ውሳኔ ላይ የሚቀርብ የክለሳ አቤቱታ የሚቀርብበት ጊዜ

- በ30 ቀናት
- የክለሳ ጥያቄ የቀረበለት ፍ/ቤት የሚወስደው እርምጃ
- ጉዳዩ ለችሎቱ ሊቀርብ አይገባም ወይም ለክለሳ በቂ ምክንያት የለም ብሎ ካመነ መዝገቡን ወዲያውኑ መዝጋት ይችላል፡፡
- ቅሬታ የቀረበበት የአስተዳደር ተቋም በአስራ አምስት (15) የሥራ ቀናት ውስጥ የጽሑፍ መልስ እንዲያቀርብ ያዛል።
- ከጉዳዩ ጋር የተያያዙ  አስፈላጊ ሰነዶች እንዲቀርቡለት ማዘዝ ይችላል። (15)

# የክለሳ ውሳኔ አሰጣጥ

- በተቻለ መጠን በአጭር ጊዜ ውስጥ መርምሮ ውሳኔ መስጠት አለበት።
- ፍ/ቤቱ ሊያፀና ወይም ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ሊሽር ይችላል።
- ፍ/ቤቱ ውሳኔውን በሙሉ ወይም በከፊል ሲሽር የአስተዳደር ተቋሙ ግድፈቶችን አስተካክሎ
  - መመሪያውን እንደገና እንዲያወጣ ወይም እንዲያሻሽል፣ ወይም
  - ውሳኔ ሰጥቶበት የነበረውን ጉዳይ እንደገና መርምሮ እንዲወስን ሊያዝዘው ይችላል።

# የክለሳ ውሳኔ አፈጻጸም

- ወዲያውኑ ተፈፃሚ ይሆናል።
- የአስተዳደር መመሪያውን ወይም ውሳኔው እንዲሻሻል ካዘዘ የአስተዳደር ተቋሙ በዚህ አዋጅ ክፍል ሁለት እና ሦስት የተመለከቱትን የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎች እና መርሆዎች አክብሮ መመሪያውን ወይም የአስተዳደር ውሳኔውን በተገቢው ጊዜ ማሻሻል አለበት።
- የአስተዳደር መመሪያ ወይም ውሳኔ በሙሉ ወይም በከፊል የመሻር ውሳኔ ወይም የማሻሻል ትዕዛዝ የክለሳ አቤቱታ የቀረበበትን መመሪያ ወይም ውሳኔ ሕጋዊ ኃይል በሙሉ ወይም በከፊል ያስቀራል።
- የአስተዳደር ተቋሙ መመሪያው ከመሻሩ በፊት በተሻረው መመሪያ መሠረት የሰጣቸው አስተዳደራዊ ውሳኔዎች እንደጸኑ ይቆያሉ።

# ተጠያቂነትና ግዴታዎች

- የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ተፈጻሚነት
- የጉዳት ካሣ
- መረጃ የመስጠት ግዴታ

============//////////
============

# እናመሰግናለን!

# THANK YOU

# GALATOO